

# ደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን

**14-16 South Morton Avenue**
**Morton, PA 19070**

## የ2022 ዓመታዊ ሪፖርት ፤ March 5th, 2023

## የይዘት ሰንጠረዥ (Table of Contents)

1. መንፈሳዊ አገለግሎት ገጽ 1

2. በጽህፈት ቤት የተከናወኑ ገጽ 1

3. የሰንበት ትምህርት ቤት ሪፖርት ገጽ 2

4. የእቅድና ልማት (ፋይናንስ) ኮሚቴ ሪፖርት ገጽ 3

5. የህንጻ ጥገናና እድሳት ሪፖርት ገጽ 3

6. የቤተ ክርስቲያን ህግ ጉዳይ ገጽ 4

7. በሲኖዶስ በኩል የተደረገ ገጽ 4-5

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

## በደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን
## የ2022 የተከናወኑ መንፈሳዊ አገልግሎቶች

1.የዘወትር እሁድ በቤተ ክርስቲያን መፈሳዊ አገልግሎት ለምእመናን በስፋት ተሰጥቷል በተለይ ስብከተ ወንጌል በተለያዩ የወንጌል መምህራን ትምህርት ተሰጥቷል

2.ዘወትር ጧት ጧት ጸሎተ ነግሀ (ኪዳን)በቀሲስ ዓለም እሸት ደርሷል

3.ለሙታን መታሰቢያ ፍትሐት ተደርጓል

4.የምክር አገልግሎት በአካል በመገኘት በስልክ እና በዙም ተሰጥቶአል

5. ዘወትር ቅዳሜ መንፈሳዊ ትምህርት ለዲያቆናትና ለእጩ ዲያቆናት ተሰጥቷአል

6.ቤተ ክርስቲያኑ ለመላው ምእመናን ክፍት ሆኖ አገልግሎት ሰጥቷል

7.የበዓለ ልደቱንና የበዓሉ ዕርገቱን የአማኑኤል ንግሥ ካህናትን በመጋበዝ በድምቀት አክብሯል

8.የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ነሐሴ ኪዳነ ምሕረትንና የየካቲት ኪዳነ ምሕረትን በዓለ ንግሥ ካህናትን በመጋበዝ በድምቀት አክብሯል

## በጽህፈት ቤት የተከናወኑ እና የተወሰኑ የ2022 ዋና ዋና ጉድዮች

1.ለቤተ ክርስቲያን ጽህፈት ቤት ካብኔቶች ተገዝተው ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ሰነድ ቤት ክርስቲያኑ ውስጥ እንዲቀመጡ ተደርጓል

2.የሰበካ ጉባኤ አባል ወ/ሮ የትምወርቅ ተካ ቀደም ብላ ትምህርት በመጀመር አይመቸኝም ስላለች በአንቀጽ 9 ሐመሩ ሐ በሚፈቅደው መሰረት አቶ መስፍን ገ/እግዚአብሔር የሰበካ ጉባኤ አባል ሆኗል

3.የ2019፣ 2020፤2021 ታክስ ሪፖርት ለIRS ከደብዳቤ ጋራ በregistered mail ተልኳል

4.የሀሳብ መስጫ ሳጥን እንዲቀመጥ ተደርጓል

# የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት የሰንበት ትምህርት ቤት
# የ2022 አመታዊ ሪፖርት

የሰንበት ትምህርት ቤታችን በዚህ ዓመት በአለ ሰንበታት እና በበዓላት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን በመገኘት

1.የዝማሬ ዓገልግሎት ሰጥተናል

2.ለምእመናኑ መዝሙሮችን በስክሪን ላይ አድርገናል

3.ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የየእለቱን ምስባክ እና ምንባባትም እንዲሁ በስክሪን ላይ ማቅረብ ጀምረናል

4.በኪዳን ጸሎትና በቅዳሴ ሰዓት መንቀሳቀስ በማይፈቅድባቸው ቦታዎች ላይ ምዕመናን ባለማወቅ እንዳይገቡና እንዳይወጡ በር ላይ በመቆም ስርዓቱን እንዲጠብቁ ለማድረግ ሞክረናል

5.በግንቦት 2015 ዓ.ም የቅዱስ አማኑኤል ንግስ በዓል ላይ በተደረገው የገንዘብ ማሰባሰብ ላይ ሰንበት ትምህርት ቤቱ $1000.00 ለመሥጠት ቃል የገባውን $100.00 ተጨምሮ $1100.00 ከአባላት ወርሀዊ መዋጮ $800.00 ታዳጊ ወጣት ዓባላት ክህጻናት ጋር በመተባበር ለ2015 ዓ.ም ዘመን መለወጫ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘምረው የሰበሰቡትን $81.00 በድምሩ $1981.00 ለደብራችን ገቢ አድርገናል

6.ከአዲስ አበባ በዙም እየገቡ በሰብከተ ወንጌል የሚያገለግሉን አባት ስልካቸው ስለተሰረቀ በደብራችን አስተዳዳሪ መልአከ ገነት ቀሲስ ዳኛቸው አሳሳቢነት የሰንበት ትምህርት ቤቱን አባላት አስተባብረን ስልኩን ገዝተናል

7.ህፃናትን መዝሙር በማስጠናት በእለተ ሰንበታት እና በበአላት ቀን እንዲዘምሩ አድርገናል

8.ከህፃናት ክፍል ሁለት ታዳጊ አባላትን ወደ ማእከላዉያን እንዲዘዋወሩ አድርገናል

የወደፊት እቅድ
የሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት እንዲሁም ህፃናት እንደየደረጃቸው መሰረታዊ የሐይማኖት ትምህርት እንዲማሩ አቅደን እየሰራን እንገኛለን

# 2022 የዕቅድና ልማት (የፋይናንስ) ኮሚቴ ሪፖርት

የእቅድና ልማት ኮሚቴ አባላት ወ/ሮ ትእግስት ዘገዬ፣ ወ/ሮ ደብሪቱ ለማ እና ወ/ሮ ሰብለወንጌል መሰረት ናቸው።

በ2022 ገንዘብ ማሰባሰብ የተደረገው ለሂተር/ማሞቂያ ማሰሪያ ነበር። በአቶ ኤፍሬም ካባ አነሳሽነትና አደራጅነት በጊቪንግ ቲውስዴይ (Giving Tuesday) $5,509.57 ተሰብስቦ ገቢ ሆኗል። በተጨማሪም በዚሁ ሂተር/ማሞቂያ ማሰሪያ ከምዕመናን $9,770 በካሽና በቼክ ለቤተ ክርስቲያን ገቢ ሆኗል። በጠቅላላው $15,279.57 ተሰብስቧል። እግዚአብሄር በረከቱን ያብዛላችሁ።

የእቅድና ልማት ኮሚቴ አባሎች እና የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ለሽያጭ አቅርበዋል። በ2022 ከንዋየ ቅድሳት ሽያጭ $3,021 ብር ገቢ ሆኗል። ቤተ ክርስቲያናችን በኢትዮጵያን ቀን በፕላኒንግ ኮሚቲ እንደተሳተፈችና በዕለቱ ካህናትና ምዕመናን እንደተገኙ ይታወቃል። በቤተ ክርስቲያኑ ስም የአበሻ ቀሚስ ለሎተሪ የሚወጣ ለኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አበርክተናል። በእለቱ ቀን ከልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ሽያጭ $1,272 ብር ገቢ ሆኗል። በአጠቃላይ በ2022 ከንዋየ ቅድሳት ሽያጭ $4,293 ብር ገቢ ሆኗል።

## የ2022 ዓመታዊ የህንፃ ጥገናና እድሳት ሪፖርት

በ2022 የአገልግሎት ዘመን የተከናወኑ ክንውኖች መካከል፡

1.የወሀ ማሞቂያ (ቦይለር) መስራት አቁሞ በአዲስ እንዲቀየር ተደርጓል

2.ከቤተ ክርስቲያን በውጪ በኩል ዙርያውን ሞሽን ዲቴክት የሚያረግ መብራቶች አምስት የኤሌክትሪክ መስመር ተዘርግቶባቸው ተገጠመዋል:: በውስጥ በኩል የተበላሸ የፍሎረሰንት በአዲስ ተቀይረዋል በዋናው በር በኩል ያለው የቤተ ክርስቲያኑ ሎጎ በመብራት የሚሰራው አስፈላጊ ጥገና ተደርጎለት እንዲሰራ ተደርጓል;

3. በቤተ ክርስቲያን ቤዝመንት ያለው አራት የተሰበሩ መስኮቶችን በተሻሻለ አዲስ መስኮቶች እንዲቀየሩ ተደርጓል

4. ከአላርም ካምፓኒ በመነጋገር በዋናው በር በኩል የሰኩሪቲ ካሜራ ተገጥሞለታል ፤ በዬል አቬኑ በኩል ያለው በር ዶርላክ አቶማቲክ ድጅታል ቁልፍ እንዲገጥም ተደርጓል

5.የቤተ ክርስቲያን ማሞቂያቅ በዘይት የሚስራ የነበረ ሲሆን የዘይት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ስለጨመረ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር አሳስቦት ምዕመናን እርዳታ አሰባስቦ በሁለት በኩል ያለውን የዘይት ማሞቂያ በጋዝ እንዲቀየር ተደርጓል

ከዚህ በተጨማሪ ብዙ አነስተኛ ጥገናዎች ማከናወናቸውን እንወዳለን

## የቤተክርስቲያን የህግ ጉዳይ

እንደሚታወቀው የሰበካ ጉባኤው ልዩ ኮሚቴ አቋቁሞ ህጉን እንዲከታተል አድርጓል። የህግ ኮሚቴ አባሎች ወ/ሮ ትእግስት ዘገዬ እና ወ/ሮ ሄርሜላ አባተ ሲሆኑ በተጨማሪም አቶ ኤፍሬም ካባ እና ዶ/ር ቅጣው ነጋሽ አብረው ያገለግላሉ።

በአማኑኤል ወኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን የህግ ጉዳይ በተመከከተ በ2022 ያለብንን የጠበቃ ክፍያ አጠናቀናል። በድሮ አማኑኤል ቤተክርስቲያን የህግ ጉዳይ በተመለከተ ለጠበቃው ይህ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩ እንደማይመለከተው አስታውቀናል።

## እስከአሁን በሲኖዶስ በኩል የተደረገ እና እየተደረገ ያለው ይሄውም በ2021 ተጀምሮ ወደ 2022 የቀጠለ የሲኖዶስ ክትትል

በሴብቴምበር 4፣ 2021 አቡነ ፊሊጶስ በሞርቶን ፓሊስ ዲፓርትመንት ተገኝተው የቤተ ክርስቲያን ቁልፍ እንዲቀየርና መልአከ ገነት እዚህ ቤ/ክ እንዳይደርሱ ማለታቸውን ታስታውሳላችሁ። ሴብቴምበር 16፣ 2021 ለብጹ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አቤቱታ አቅርበናል። አቡነ ፊሊጶስ ያደረሱብንን በደል በጽሁፍ አስረድተናል።

1) የቤተክርስቲያን በር እንዳሰበሩ

2) ባንክ ውስጥ ያለውን የሞርጌጅ ገንዘብ እንዳሳገዱብን

3) ከነበረው ሰበካ ጉባኤ ጋር አንድ ቀን እንኳን እንዳልተነጋገሩ

4) ለምዕመናን የማይጨነቁ ወገንተኛ አባት መሆናቸውንና

5) እኛ ከአሁን በኋላ እሳቸው አባት እንደማይሆኑን እና በዲሲ ሃገረ ስብከት ስር እንድንሆን አመልክተናል።

እንግዲህ እኛ እንደ ኦርቶዶክስ አማኞች ወደሲኖዶስ አቤት ስንል፣ እነሱ ደግሞ ወደ ዓለማዊው ፍርድ ቤት ሄደው ከሰውናል። ይህንን የአቤቱታ ደብዳቤ በውጪ ጉዳይ መምሪያ እና በሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ታይቷል። ከታየም በኋላ በኦክቶበር 9፣ 2021 የሲኖዶስ ጽ/ቤት

1) አቡነ ፋኑኤል የዲሲና የአካባቢው ሊቀ ጳጳስ
2) አቡነ ጴጥሮስ የሰሜን አሜሪካ ኒውዮርክ እና አካባቢው ሊቀ ጳጳስ
3) እንዲሁም ቀሲስ በላይ ፀጋዬ የሲኖዶስ ምክትል ፀሃፊ
ችግሩን አጣርታችሁ በተለያዩ ወገኖች መካከል እርቀ ሰላምን አውርዳችሁ ሪፖርት እንድታቀርቡ ብሎ ወሰነ።

በዲሴምበር 15፣ 2021 ከነዚህ ልዑካን ጋር በዙም ተነጋግረናል። በጊዜው እኛ ያነጋገርናቸው ተከሰናል። እንዲያውም በጀነዋሪ 7፣ በጌታ ልደት ቀን ፍርድ ቤት እንድንቀርብ ታዘናል። በመሆኑም፣ ከእናንተ ጋር ዲቴይል ማውራት አንችልም። ይህ ከሃገሩ ህግ ጋር አይሄድም። ጠበቃችንም ይህንን አይደግፉም። ስለዚህ ያለን አማራጭ ሁለት ነው።

1) ክሱን ያቁሙና መነጋገር
2) ከጀነዋሪ 7 በሗላ ግዜ ስጡን እና እንነጋገር ነው ያልናቸው።
ከዛ እንደምታውቁት ጀነዋሪ 7 ፍርድ ቤት ቀርበን በጀነዋሪ 10 ለኛ ተፈረደልን።
በፌብረዋሪ 2፣ 2022 ለነዚሁ ልዑካን ያለንን ማስረጃ አያይዘን በምክትል ጸሃፊው በኩል እንዲደርስ አድርገናል።

የደብዳቤው ሶስት ዋና ሃሳቦች
1) ልዑካኑ ከተመደቡ በሗላ አቡነ ፊሊጶስ በፖሊስ አስገድደው ቤ/ክ ለመግባት እንደሞከሩ
2) ፍርድ ቤቱ ለኛ እንደፈረደል እና
3) ያለ አግባብ የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳዳሪ ላይ የጣሉትን የስልጣነ ክህነት እገዳ እንዲነሳልን ጠይቀናል።

በማርች 18፣ 2022 ለብፁ አቡነ ማትያስ የመልአከ ገነት የስልጣነ ክህነት እገዳ እንዲነሳልን ጠይቀናል።
በጁን 3፣ 2022 ለመልአከ ገነት የተጻፈው ደብዳቤ ለሰበካ ጉባኤው ሪፖርት ተደርጓል። ይሄም ደብዳቤ የሚለው፣ የጳጳሱን መመሪያ እየተቀበሉ እንዲያገለግሉ እናስታውቃለን ነው።
በጁላይ 12፣ 2022 ሰበካ ጉባኤው ለፓትርያርኩ መልስ ሰጥቷል። ያለውም፣ በሲኖዶስ የምንመራ እና የቅዱስ ፓትርያርኩን ትዕዛዝ ለመፈጸም ዝግጁ እንደሆንን ነገር ግን አቡነ ፊሊጶስ በአሜሪካን ሃገር ህግ መሰረት እዚህ ቤ/ክ መግባት እንደማይችሉ ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ ጋር አያይዘን ልከናል። በተጨማሪም አሁንም በዲሲ ሃገረ ስብከት እንድንመደብ ጠይቀናል በሴብቴምበር 22፣ 2022 መልአለከ ገነት በአስቸኳይ ወደ ሲኖዶሱ እንዲመጡ የሚል ደብዳቤ ደረሳቸው።

በሴብቴምበር 28፣ 2022 ለጥሪው መልስ ተሰጥቶ ተልኳል። ይህውም የጉዞ ሰነድ ስለሌለኝ በማንኛውም ጊዜና ሰዓት ዘመኑ በሚፈቅደው ቴክኖሎጂ ቀርበው ለማስረዳት ዝግጁ እንደሆኑ የሚገልጽ ነበር

እንግዲህ ከዛ በሗላ የዚህን ደብዳቤ መልስ ነበር የምንጠብቀው። እሺም እንቢም ሳይሉ ለሲኖዶሱ ምልዓተ ጉባኤ ሳይደርስ "የሲኖዶሱን ጥሪ ስላልተቀበሉ ቀርበው እስከሚያስረዱ ድረስ ስልጣነ ክህነትዎ ተይዟል" የሚል መልዕክት መጣ ተባለ። ይህም ለኛ እስካሁን ያልደረሰን ደብዳቤ ነው።

እኛ ግን አባቶችን ስናነጋግር የእኛ ጉዳይ አጀንዳ እንዳልተያዘለትና እንዳልተነጋገሩበት ነው ያስረዱን። እንዳያችሁትም አቡነ ጴጥሮስ ከአቡነ አብርሃም ጋር ሆነው እንደወሰኑ ነው የተረዳነው። አሁንም አቤት ወደሚባለው ቦታ ሁሉ አቤት ለማለት በዝግጅት ላይ ነን።
ወስብሃት ለእግዚአብሄር